የሰ/መ/ቁ. 63635

ሰኔ 27 ቀን 2003

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ጉልላት ወልዴ ጠበቃ ሰይፈ ረታ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ነገረ ፈጅ ገ/ማርያም ዋዴሮ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ከሣሽነት የተጀመረ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ከሣሽ በተከሣሽ ድርጅት በወር ብር 2847 እየተከፈላቸው ሲሰሩ ቆይተው ያላቸው የሥራ ውል በጡረታ ምክንያት ከሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የተቋረጠ መሆኑን ገልፀው ከሥራ ከመገለሌ ጋር ተያይዞ ሊከፈለኝ ከሚገባው የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ብር 7051.49 ስላስቀሩብኝ ለዚህ ክስ ያወጣሁት ወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር መልስ የሠጡ ሲሆን ቀርቦ የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ከሣሽ ከሥራ የተሠናበቱበትና ክስ ያቀረቡበት ጊዜ መካከል ከ6 ወራት በላይ ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል ነው፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ከካራከረ በኋላ ከሣሽ ከሥራ በጡረታ ከተገለሉበት ቀን ሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም መካከል ያለው ጊዜ በአዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 162/4/ የተደነገገውን የይርጋ ዘመን ደንብ የሚፃረር በመሆኑ እና በወቅቱ የቀረበ ክስ ባለመሆኑ በይርጋ ውድቅ ይሆናል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 337 መሠረት አፅንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን አመልካች ታህሣሥ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገፅ ጽፈው ያቀረቡት የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ተጠሪ ያለበትን የክፍያ ጥያቄ ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ያመነ ሲሆን በአሁኑ አመልካች መተማመኛ ያልተደረገበትን ዕዳ ተቀናሽ በማድረግ ክፍያ የፈፀመው ደግሞ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በመሆኑ ይርጋው የተቋረጠ መሆኑን እየተከራከርኩ ውድቅ መደረጉ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል

በመባሉ ተጠሪ የካቲት ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገፅ ፅፎ መልስ የሠጠ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ አመልካች ይርጋ ቀሪ ስለሚሆንበት አግባብ በሥር ፍርድ ቤት ያልተከራከረ በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አዲስ ክርክር ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረቡትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም የቀረበው የክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች ለቀረበበት የይርጋ ተቃውሞ ይርጋው ሊቋረጥ ይገባል የሚለውን መከራከሪያ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቧል ወይስ አላቀረበም? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ አመልካች ይርጋውን ሊያቋርጥ ይችላል ብሎ የሚከራከረውን በተጠሪ የተፃፈ ደብዳቤ ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረበ በመሆኑ ፤ ከዚያ በመቀጠል የይርጋ ተቃውሞ በተጠሪ ሲቀርብበት ተጠሪ ያለበትን ክፍያ በማረጋገጥ የፃፈው ደብዳቤ ይርጋን ያቋርጣል በማለት የተከራከረ መሆኑን ችሎቱ ተረድቷል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክር እያቀረበ ነው የሚባል አይደለም፡፡ ይልቁንም በበታች ፍርድ ቤት ሲያነሣው የነበረ እና ፍርድ ቤቱ ሣይመለከተው ያለፈው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑ በሰበር ሰሚ ደረጃ የተነሣ አዲስ ክርክር ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል የአመልካችን ክርክር አግባብነት ስንመለከት በእርግጥ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162/4/ መሠረት ከሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር ተያይዞ ሊከፈለኝ የሚገባ ክፍያ አለኝ በማለት የሚቀርበው ክስ በ6 ወር ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ተጠሪም እየተከራከረ ያለው አመልካች በጡረታ የተገለለበት ጊዜ እና ክስ ያቀረበበት ጊዜ መካከል ያለው ጊዜ ከ6 ወራት በላይ ሆኖአል የሚል ነው፡፡ ይሄንን የይርጋ ተቃውሞ በተመለከተ አመልካች ከበታች ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ እየተከራከረ ያለው ተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ የይርጋ ዘመኑ ይቋረጣል በሚል ነው፡፡ ይሄንን በተመለከተ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጠሪ ተፃፈ በማለት የተነሳው ነጥብ ስለመፃፍ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ በዚህም ደብዳቤ ለአመልካች የሚከፈል ክፍያ እንዳለና ሆኖም የሚቀናነሱ ክፍያዎች በዚሁ ደብዳቤ የተገለፁ መሆኑን ችሎቱ ተረድቷል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 164/3/ መሠረት ይርጋን ለማቋረጥ ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ ይርጋው በዚሁ ደብዳቤ ይቋረጣል ብለናል፡፡ ይርጋ ዘመን ከተቋረጠ ደግሞ አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ ስለዚሁ የሚደነግግ የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1852/1/ ሥር የተደነገገ በመሆኑ ከጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ጊዜውን ስንቆጥር ክስ እስከቀረበበት ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ 6 ወራት ያላለፈው በመሆኑ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም ብለናል፡፡

በዚሁ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው መወሰን ሲገባው የቀረበው ክስ በይርጋ ውድቅ ነው በማለት መወሰኑና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይሄንን ሣያስተካክል ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ 96677 በቀን 02/03/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 33762 በቀን 07/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ስለማይሆን በፍሬ ጉዳይ ተገቢውን ማጣራት ከተደረገ በኋላ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲሠጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ላይ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ከፌ/የመ/ደ/ፍቤት የመጣው የመዝ.ቁ . 33762 ወደ መጣበት ይመለስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ